# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
# The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org

1) **መመኪያዬ አንተ ነህ**
መመኪያዬ አንተ ነህ የነፍሴ መዳኛ
ተመልከት ወደኔ አትስጠኝ ለዳኛ
ሕይወቴን ላንተ (2) ብያለሁ
አምላክ የኔ ጌታ የት አገኘሀለሁ
ከበደሌም አንጻኝ ደግሞም ከኃጢአቴ
በመንፈስ ይታደስ መላ ሰውነቴ
ሕይወቴን ላንተ.......
አቀበቱ ልቤ በጭንጫ ትዕቢት
አሸብርቆ ነበር አልፈርስም መስሎት
ሕይወቴን ላንተ.........
የጾም ንጉስ መምጣት ስለተነገረ
መደልደል አለበት እየተሰበረ
ሕይወቴን ላንተ.......
ሶስናን ያዳንካት ከሀሰት ምስክር
እኔንም አድነኝ ካልታሰበ ነገር
ሕይወቴን ላንተ

2) **ሰላም ሰላም**
ሰላም ሰላም ብለን እንዘምር ስሙን
ተአጋሽ ነውና የዓለም መድኅን (2)
ሰማይን በብርሃን አስጊጦ ሠርቷት
ምድርን በውኃ ላይ አጽንቶ ፈጥሯት(2)
እጅግ ድሀ መሳይ የንጉሥ ልጅ ንጉሥ
ባህያ ተቀምጦ ገባ ከመቅደስ (2)
በገዛ ገንዘቡ ውኃ ጥም ይዞት
ተጠማሁ ቢላቸው ሀሞት አጠጡት (2)
የሕይወት ምንጫችን እንዳልሆነ ሁሉ
ውኃ ስጡኝ ብሎ ለመነ በቃሉ (2)
እጅግ ያስደንቃል የሱ ትእግስት
ቃልም አልመለሰ እንዲያ ሲገርፋት (2)
ዘጠና ዘጠኙን መላእክትን ትቶ
ቆሟል ቀራንዮ እንጨት ተጠግቶ (2)

3) **እስመ ለዓለም**
እስመ ለዓለም ምህረቱ (2)
አያልቅም ብዙ ነው ያምላክ ቸርነቱ (2)
አመስግኑት ጌታን ሁላችሁ ባንድነት (2)
መሐሪ ነውና ለሰው ልጆች ሕይወት (2)
እስመ ለዓለም.........
የማይሞተው ሞቶ የተቀበረው (2)
ከገሃነም እሳት እኛን ሊያድን ነው (2)
እስመ ለዓለም........
ከማርያም የነሳው ያ ቅዱስ ሥጋው (2)
ቀራንዮ ሲውል የሚያሳዝን ነው (2)
እስመ ለዓለም........
በፈጠረው ፍጥረት እጅግ ተሰቃይቶ
ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል ጐትቶ
እስመ ለዓለም........

4) **አምላክ ሆይ ወደኛ**
አምላክ ሆይ ወደኛ ባትመጣ ለብሰህ የማርያም ሥጋ
ባክኖ የነበረው ያዳም ዘር ውጤቱ ነበር የሚያሰጋ
በዚያ ዓመት በዚች ወር በዚያች ቀን ድኅነትን ለሰው ልጅ ስትሰጥ
ምን የበዛ ነበር ትህትና ትዕግስትህ የማይለወጥ
የሾህ አክሊል ደፍተው በራስህ ጐንህን ሲወጉ በጦር
አንተ ግን ለእነርሱ ካባትህ ምሕረትህን ትለምን ነበር
ግን መቼ ዐወቁ እነርሱ በኀጢአት ደንድኖ ልባቸው
መድኃኒታቸውን ገረፉህ ሰቀሉህ አንተም ሞትክላቸው
ዳግም ስትመጣ ለፍርድ ከዓለም ፍጻሜ በኋላ
ኧረ እንዴት እድለኞች ናቸው በፊትህ የሚያገኙ ተድላ
በዚያች በደብረ ዘይት ቦታ ደስታና ለቅሶ ሲፈልቅ
ከቶ ከየት ይሆን እጣዬ ያን ጊዜ የእኔ አወዳደቅ
የጸጸት እሮሮ በፊትህ እንዳያቃጥለኝ እኔን
እርዳኝ ፈጣሪዬ ከአሁኑ አድሰው የዛገው ልቤን

5) **ቃል ሥጋ ለበሰ**
ከሶስት አካል አንዱ ቃል ሥጋ ለበሰ
ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን
አዳም በበደለ መድኃኔዓለም ካሰ
ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን
በኛ በኃጢአት እርሱ ተከሰሰ
ማረን ይቅር በለን
ሁሉን የምታውቅ የዓለም ጌታ
እግዚኦ እግዚኦ
አልፋና ዖሜጋ የዓለም ቤዛ የዓለም ፈውስ
እግዚኦ እግዚኦ
ሞትን አጠፋልን ሰጠን አዲስ ሕይወት
ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን
ባለ ተስፋ አረገን ለዘላለም ንብረት
ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን
በደሙ ዋጀልን አዲስ ሥነ ሥርዓት
ማረን ይቅር በለን
ሁሉን የምታውቅ የዓለም ጌታ
እግዚኦ እግዚኦ
አልፋና ዖሜጋ የዓለም ቤዛ የዓለም ፈውስ
እግዚኦ እግዚኦ
ተወቅሰ ቆሞ ከጲላጦስ ደጃፍ
ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን
ከትዕግስት በቀር አላሳየም ጸያፍ
ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን ማረን
አምላክ በመሆኑ አነጻን ከእድፍ
ማረን ይቅር በለን
ሁሉን የምታውቅ የዓለም ጌታ
እግዚኦ እግዚኦ
አልፋና ዖሜጋ የዓለም ቤዛ የዓለም ፈውስ
እግዚኦ እግዚኦ

6) **አታውኪኝ ነፍሴ**
አታውኪኝ ነፍሴ አታስጨንቂኝ
በዓለም መድኃኒት በእግዚአብሔር ታመኚ (2)
ዋልያ እንደሚናፍቅ ወደ ውኃ ምንጮች
አቤቱ ወዳንተ ነፍሴ ናፈቀች (2)
አታውኪኝ ነፍሴ...............
መቼ ተነስቼ መቼ እደርሳለሁ
ያምላኬንስ ፊቱን መቼ አየዋለሁ (2)
አታውኪኝ ነፍሴ...............
የሕይወትን ውኃ እያስታወሰች
ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች (2)
አታውኪኝ ነፍሴ...............

7) **በጌቴ ሰማኒ**
በጌቴ ሰማኒ ባታክልቱ ቦታ (2)
ለኛ ሲል ጌታችን ባለም ተንገላታ (2)
አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት (2)
ለኛም ነበረብን የዘላለም ሞት (2)
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ (2)
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ (2)
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ (2)
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ (2)
በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው (2)
እምዲህ ሲል ጸለየ አባት ማራቸው (2)
በረቂቅ ሥልጣኑ ሁሉን የፈጠረ (2)
በሰዎች ተገርፎ ሞተ ተቀበረ (2)
ፍቅሩን የገለጸው ተወልዶ በሥጋ (2)
ኢየሱስ ጌታ ነው አልፋና ዖሜጋ (2)

8) **ምን ሰጡህ**
ሙትን ልታስነሳ ድውይን ልትፈውስ
ሥልጣን ሰጥቶህ ነበር ኢየሱስ ክርስቶስ
ልታስር ልትፈታ በነፍስም በሥጋ (2)
ሥልጣን ሰጥቶህ ነበር አልፋና ዖሜጋ (2)
ምን ሰጡህ ይሁዳ አይሁድ ወገኖችህ
ለነርሱ አሳልፈህ ጌታህን የሰጠህ
ከሁሉ የሚበልጥ ሥልጣን ሰጥቶህ ሳለ (2)
ብርን ለመቀበል ልብህ ተታለለ (2)
ሰማይና ምድርን በቃሉ የፈጠረ
እንዴት በመቃብር ሶስት ቀን አደረ
አንተ የሰጠኸው አሳልፈህ ለሞት(2)
ሞትን ድል አድርጎ ተነሳ በሰንበት (2)

9) **አልፋና ዖሜጋ**
አልፋና ዖሜጋ ፈጣሪ የሆንክ
በከሃዲዎች እጅ ተይዘህ ቀረብክ
ተገፉህ ተደፋህ በጥፊ ተመታህ
እየደበደቡህ ክርስቶስ ሆይ አሉህ
ጽድቅን ስለሰራህ በወንጀል ከሰሱህ
ላዳም ቤዛ ብለህ ብዙ ተንገላታህ
አልፋና ዖሜጋ...............
ቅዱሳን እጆችህ የፊጥኝ ታስረው
እንደበግ ተጎተትክ ብትምራቸው
የትም ቦታ ያለህ ሁሉን የምታውቅ
ፊትህን ሸፈኑት ለመመጻደቅ
አልፋና ዖሜጋ.................
በዓውደ ምኩናን ከጲላጦስ ዘንድ
አሳልፈው ሰጡህ አጋልጠው ለፍርድ
ከሃና ቀያፋ ከካህናቱ ደጅ
ከነሄሮድስ ዘንድ አቀረቡህ ባዋጅ
አልፋና ዖሜጋ.......
ግርፋት ሕማሙ አልበቃ ብሎህ
በመስቀል ላይ ልትውል ተፈረደብህ
ሳዶርና አላዶር ዳናትና ዴራ
ተፈልገው መጡ ለችንካር በተራ
አልፋና ዖሜጋ.........
የሰላም ባለቤት ደረትህ ተወጋ
ሊያያዝ በችንካር እጅህ ተዘረጋ
ግፈኞች አይሁዶች ባንተ ላይ ቀለዱ
ምራቅን ተፉብህ እራስክን ሊጎዱ
አልፋና ዖሜጋ.............

10) **የአብርሃም አምላክ**
የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ቤዛ(2)
ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ(2)
የሐሰት ምስክር አቁመው ከሰሱት(2)
በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት(2)
ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አስሮ(2)
ከሮማዊው ንጉስ እንዲኖር ተፋቅሮ (2)
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ(2)
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ(2)
በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ (2)
በችንካር ላይ ቆመው ምንም አልሰለቹ(2)
የብርሃን አክሊልን ለሰማዕት ያደለ(2)
የሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ። (2)

### 11) አምላክ ለኛ ብሎ

አምላክ ለኛ ብሎ ብሎ ቢያፈሰው ደሙን
ለምን ከለከለች ጸሀይ ብርሃኗን
የከበረው ሥጋ የከበረው ደም
በመስቀል ላይ ዋለ በኢየሩሳሌም
እዩት ኢየሱስን መስቀሉ ማማሩ
ለተመራመረው ብዙ ነው ምስጢሩ
ቢመቱት ቢሰቅሉት ቢያላግጡበት
ምንም አላገኙም ከርሱ ዘንድ ስሕተት
ፈጣሪ መሆኑን ምስጢሩ ገብቷት
ጌታን አልይዝ አለች ግዑዟ መሬት
እዩት ኢየሱስን..........
ይህ ትልቅ ንጉሥ ሲገለጽ በሰማይ
የናቁት የወጉት ይሉሰታል ዋይ ዋይ
ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሲሸሹ
ወዴት ልግባ ይላል ትልቁ ትንሹ
እዩት ኢየሱስን..........
ወደ ሰማይ ያረገው የከበረው ሥጋ
ዳግመኛ መምጣቱን ሁላችን እንዘንጋ
በሰማይ ለሚኖር ቅዱስ አባታችን
ምስጋና ይድረሰው ከኛ ከሁላችን
እዩት ኢየሱስን

### 12 ጌታ ሆይ

ጌታ ሆይ አይሁድ አማጽያን ሰቀሉህ ወይ
የዓለም መድኃኒት የዓለም ሲሳይ ሰቀሉህ ወይ (2)
የአዳም በደል አደረስህ አንተን ለመሰቀል
የሔዋን ስህተት አበቃህ ለሞት ቸሩ አባት (2)
ንጹህ ክርስቶስ ሆንክ በደለኛ ብለህ ስለኛ
መስቀል አሸክመው አስረው ገረፉህ እያዳፉህ (2)
እጅና እግርህ በብረት ተመታ የዓለም ጌታ
የሾህ አክሊል ደፍተህ ጎንህን ተወጋህ አልፋና ያሜጋ (2)
ግብዞች እንደረሳቸው መስሎአቸው
ምራቅ እየተፉ በፊትህ ቀለዱ አንተን ሊጎዱ (2)
በመስቀል ላይ ተጠማሁ ስትል ታላቅ በደል
ሐሞትና ከርቤ ሰጡህ ቀላቅለው ጠጣ ብለው (2)
ይቅር ባይ ግልጽ በደላችንን ሁሉን ሳታይ
አንተ ይቅር በለን በኛ ሳትከፋ (2)

### 13) ሞተሃልና ስለኔ

ሞተሃልና ስለኔ ምንም ሳይኖርብህ ጥፋት
ተከስህ ተወቅሰህ በጲላጦስ ፊት
ኢየሱስ አምላከ ምሕረት ስብሐት ለከ።
ያንተ መንገላታት ሁልጊዜ ያሳዝነኛል ሲወራ
በመስቀል ላይ ሆነህ ያየኸው መከራ
ኢየሱስ ሕይወት እንጀራ ስብሐት ለከ።
ከልዑል ቦታ ዝቅ ብለህ ፈጣሪ ፍጡራን አምላክ
በሰው ፊት ተዋርደህ ስለሰው የሞትክ
በመስቀል ላይ ተጠማሁ እያልክ ስብሐት ለከ።
ክፉ አድራጊዎች ተነስተው በምቀኝነት መንፈስ
ብዙ ሲጣጣሩ ለደምህ መፍሰስ
ሞትክላቸው ደስ እንዲላቸው ስብሐት ለከ።
መሀሪ ጌታ አሁንም እንደ ቸርነትህ ብዛት
የኛን በደል ሁሉ ሳትመለከት
አድነን ከዳግም ሞት ስብሐት ለከ።

### 14) ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን

ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን አባት ሆይ በመስቀልህ ሆነህ (2)
ድምጽህን በማሰማት አባት ሆይ ነፍስህን ሰጠህ (2)
የሰማይ ከዋክብት በሙሉ ረገፉ
ጨረቃና ፀሐይ ደምን አጎረፉ
ብርሃናት ጨለሙ ጠፍተው ተለያዩ
ሥጋህን በመስቀል ተገልጦ ስላዩ
ዘጠኝ ሰዓት........
ጌታችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ
አሰምቶ ጮኸ ተጠማሁ እያለ
ማርና ወተትን ለሚመግበው
ሐሞት አመጡለት ይቅመሰው ብለው
ዘጠኝ ሰዓት...........
አካሉ ሲወጋ ውኃ ደም ፈሰሰ
በምድር ተረጭቶ ዓለምን ቀደሰ
የእስራኤል ሴቶች ዋይ ዋይ ሲሉልህ
ለነሱ አዘንክ እንጂ ላንተስ አላሰብህ
ዘጠኝ ሰዓት.............
እናትህ ስታለቅስ በመስቀል ስር ሆና
ዮሐንስ ሰጠህ ጠብቆ እንዲያጽናና
መላእክትም ታዩ አጋንንትም ሸሹ
የአይሁድ ሰራዊት ፈርተው ተረበሹ
ዘጠኝ ሰዓት............

### 15) ፀሐይም ጨለመች

ፀሐይም ጨለመች ጨረቃም ደም ሆነች
ያልበደለው ንጉስ ተሰቅሎ ስላየች
ዋ እኔን (2) ለኛ ይገባል ለቅሶ
በኛ በደል እርሱ አካላቱን ክሶ
ጠላቶቹን ሁሉ ከማጥፋት ታግሶ
እነሆ ተሰቅሏል ከለሜዳ ለብሶ
ክርስቶስ ንፁህ ሲሆን ቅዱስ ሲሆን ሐሰት ሳይኖር በቃሉ
እነሆ እዩት ተሰቅሎ ደሙ ይዘንባል ከአካሉ
የሚያምንበት ሰው ሊያድነው ነው አሉ
ቤዛቸው ነውና ለዓለሙ ሁሉ
ስለኛ ተሰቀለ እንዲሁም ሞተልን
በበደልነው ክሶ እኛን ሊያድነን
ፀሐይም ጨለመች ጨረቃም ደም ሆነች
ያልበደለው ንጉስ ተሰቅሎ ስላየች።